[illegible]

ለራድዮ ሰላም ድርብ ተልእኮ፣ ድርብ ኪሣራ ሴፕቴምበር 3/1994

~~ሽግግሩና በአጋጣሚ የተቀጨ ተስፋ~~

የደርግ አገዛዝ ወድቆ ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ሃገራችን ከዘመናት የጦርነት ጉዳት ተላቃ የሰላምን ጸጋ የምትቀምስበት፣ ከዘመናት የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ተላቃ ዲሞክራሲን የምትጎናጸፍበት አዲስ ሂደት ይጀመራል የሚል ተስፋ በአንዳንድ ኢትዮጵያውያንና ለሃገራችን በጐ በሚመኙ የውጭ ወዳጆች አካባቢ ፈንጥቆ እንደነበረ የሚታወስ ነው::እርግጥ ኢህአዴግ ለዚህ ከባድ ታሪካዊ ተልእኮ ብቁ መሆኑን የሚጠራጠሩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች ነበሩ:: 'ነጻ አውጭ' ነን በሚሉ ንቅናቄዎች ታሪክ የትም ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ ይህ ድርጅት አዲስ አበባን ነጻ አወጣሁ ብሎ ሲቆጣጠር የከተማው ህዝብ በሆይታና በእልልታ ሳይሆን በተቃውሞ ሰልፍ መቀበሉ የዚህ ጥርጣሬ ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው:: ዛሬ ኢህአዴግ ራሱ ለራሱ በቀየሰው ሂደት፣ ራሱ ለሽግግሩ በሰጠው ወልጋዳ ትርጓሜና ተልእኮ አማካኝነት የተሳካ ሽግግር አካሄዱኮ አገባደድሁ እያለ የሚመጻደቅበት ወቅት ውስጥ ገብተናል:: በሌላ በኩል ደግሞ ከመጀመሪያውም የኢህአዴግን ብቃት የተጠራጠሩት ዜጎች በመላው ህብረተሰብ ታጅበውና ተጠናክረው የዚህን የሽግግር ሂደት ኪሳራ በመመዝገብ ለሌላ የታሪክ ምእራፍና ለሌላ ብሄራዊ የነጻነት ተጋድሎ የሚዘጋጁበት ወቅት ውስጥ እንገኛለን::

በአንድ በኩል በኢህአዴግ በሌላ በኩል ደግሞ በህብረተሰቡ መሃከል በዚህ ጉዳይ የተከሰተው ልዩነት በሁለቱ ክፍሎች መሃከል ስለሽግግሩ ምንነትና ስለ ታሪካዊ ተልእኮው ከፍተኛ የአስተያየት ልዩነት በመኖሩ ነው ብለን እንገምታለን::

የፖሪሱ የሰላምና እርቅ ጉባኤ ተሳታፊ ድርጅቶች ተወካዮች ለአዲስ አበባው ጉባኤ ባቀረቡት የመንደርደሪያ ሰነድ ስለዚህ የሽግግር ዘመን ያላቸውን አስተሳሰብ በምንም ዓይነት በማያሻማ ሁኔታ አቅርበው እንደነበረ የሚታወስ ነው:: ሰነዱ የዚህን የሽግግር ዘመን ተልእኮ አስመልክቶ ያሰፈረው አስተያየት በሁለት የሚከፈል ነበር:: በአንድ በኩል ከአጭር ጊዜ አንጻር ሲታይ ለዚህ የሽግግር ሂደት ጠባብ ትርጉም እንዳይሰጠውና ህብረተሰቡን እንዳለ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገሪያ እንጂ የአንድን ቡድን ወይም ድርጅት የሥልጣን ጥም ማርኪያ መሣሪያነቱ ብቻ እንዳይተረጐም ያስጠነቅቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሃገራችንን ለዘመናት አውተብትበው የያዟት የሰላም ጠንቆች እጅግ ሥር የሰደዱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ስነልቡናዊ ሥረ መሠረቶች ስላሏቸው የሽግግሩን ዘመን እነዚህን ጠንቆች ለመዋጋት የምንጀምርበት የተሃድሶ ዘመን ሆኖ እንዲታይ ጥሪ ያቀርባል

ከነዚህ ግልጽ ተልእኮዎች አንጻር ሲታይ የሽግግሩ ወቅት ሙሉ በሙሉ ከሽፏል ማለት ይቻላል::

የመጀመሪያውን ተልእኮ አስመልክቶ ይህ የሰባቱ ድርጅቶች ተወካዮች ያቀረቡት ሰነድ እንደሚከተለው ብሎ ነበር፣

"ዛሬ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትና ህዝቧም በጉጉት የሚጠብቀት ሽግግር አንድ መንግሥት ሌላውን የሚተካበት፣ አንድ የፖለቲካ ኃይል በሌላው የሚለወጥበት፣ ወይም ደግሞ አንድ ጊዜያዊ መንግሥት ወደ ቋሚነት የሚሸጋገርበት ሂደት ብቻ አይደለም::

"የሚያስፈልገን ህብረተሰቡ በሙሉ ከአንድ ጸረ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደ ተሻለና የመላውን ህዝብ ተቀባይነት ወዳገኘ ሥርዓት የምንሄድበት ሽግግር ነው:: በሁለቱ አስተሳሰቦች መሃከል ይህ ነው የማይባል ልዩነት አለ::

"በጸረ ዲሞክራሲያዊ ሂደት፣ በይስሙላ ህገመንግሥት፣ በተጭበረበረ ምርጫ፣ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ይህንን ሁሉ በጊዜያዊ ወታደራዊ የበላይነት አስመርኩዞ አንድ ጊዜያዊ መንግሥት ራሱን ወደ ቋሚነት ሊያሸጋግር ይችላል:: ህብረተሰቡን ሳይዝ:: ብቻውን:: ይህ

ግን ኢትዮጵያ ካለፈው በሃይል የበላይነት ብቻ ከፈለቀ ጸረ ሰላምና ጸረ ዴሞክራሲ ስርዓት ወደ አዲስ ስርዓት ተሸጋገረች ማለት እንደማይሆን ግልጸ ነው:: ያለ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር ይቻላል ማለት ዘበት ነውና::

"አጨፋሪና ጥቃቅን የሆኑ ክስተቶችን ወደጐን ብንተዋቸው ዛሬ በህብረተሰቡ ፊት የተደቀኑት ሁለት መሠረታዊ አማራጮች እነዚህ ብቻ ናቸው::"

ዛሬ የሽግግሩ ዘመን እያከተመ ባለበት ወቅት የኢህአዴግ መሪዎች የትኛውን አማራጭ እንደያተክተሉ ሆነ ግልጸ ነው:: ጠባቡን የሥልጣን ቅብብሎሽ፣ ከሣራውን ጠባብ ሂደት፣ አደገኛውን ጸረ ዴሞክራሲያዊ ጐዳና ለህዝብና ለወገን ምንም ደንታ በሌለው ሁኔታ በሃይል በህብረተሰባችን ላይ ጭነዋል:: ኢህአዴግ በስት ዓመት ሙሉ ነገሮችን ካመቻቸ በኋላ ራሱ በራሱ ባዘጋጀውና ብቻውን በተወዳደረበት ምርጫ አማካኝነት 90 ከመቶ በአሸናፊነት ወጣሁ ብሏል:: ከዚህ "ምርጫ" ከተባለ ነገር ፈለቀ የተባለው የኢህአዴግ መደበኛ ድርጅታዊ ጉባኤ 'ህገመንግሥት ጉባኤ' የተባለ ስያሜ ተሰጥቶት በህገመንግሥታት ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ የአንድ ድርጅት የፖለቲካና የርእዮተዓለም አቋም የአንድ ሃገር የበላይ ህግ ተብሎ ሊታወጅ ዝግጅት እየተደረገ ነው:: ዓለመኛው አቶ መለስ ዜናዊ ካለፉት መንግሥታትም ሆነ ከዛሬይቱ አፍሪካችን ታሪክ ምንም የቀሰመው ትምህርት ስለሌለው ይህንን ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር አብሮ በስመጥፋነት የሚከስም ሰነድ ከዛሬው ትውልድ ዘልቀ ለሚከተለውም ትውልድ የሚተላለፍ ታሪካዊ ሰነድና የኢትዮጵያ የበላይ ህግ ይሆናል ብሎ እስከመተንበይ ደፍሯል::

በዚህ ህብረተሰቡን ወደተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገር ተልእኮ አንጻር የደረሰውን ኪሣራ ለማብራራት መሞከር ለቀባሪ አረዱት ዓይነት ስለሚመስለብን ብዙም አናትትበት:: ይህም ሆኖ የሽግግሩ ሂደት በዚህ ጠባብና የሥልጣን ጥም በማርኪያ ገጸታው በመተርጎሙ በህብረተሰቡ ላይ ሊደርስ ስለሚችለው አደጋ አሁንም ሰነዱን በመጥቀስ ለመጠቆም እንገደዳለን:: የሰላምና እርቅ ጉባኤ አስተባባሪ ኰሚቴ ይህ የኢህአዴግ ጸረ ዴሞክራሲና ጸረ ሰላም የሽግግር ሂደት ሊያስከትል ስለሚችለው የጥፋት ጉዞ ሲያትት እንደሚከተለው ብሎ ነበር፣

"ኢህአዴግ ወደዘላቂና ቋሚ መንግሥት ለመሸጋገር የሚያደርገው ጥረት በቀጠለ ቁጥር ጸረ ዴሞክራቲክ አሠራሩ እየተፋፋመ፣ ይህ ደግሞ ይበልጥ ተቃውሞን እየቀሰቀሰበት፤ ይህንንም ለመቋቋም ጸረዴሞክትና ጸረ ሰላም ርምጃዎችን እያበራከተ የሚሄድበት አዙሪት ውስጥ ራሱን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ይዘ የሚነጉድበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለን እንሰጋለን::"

ነገር ግን ለሃገራችን ሰላም ከፍተኛ አደጋ የሚፈጠረው በዚህ በጸረዴሞክራሲያዊ ሂደት አማካኝነት ለአንድ ፈላጭ ቆራጭ አናሳ ኃይል አገዛዝ መዳረጋችን ብቻ አይደለም:: ከዚህ ባላነሰ የሚያሰጋን የፖሪሱ ድርጅቶች ተወካዮች ስለሽግግሩ ታሪካዊ ተልእኮ ጠቁመውት የነበረው ሁለተኛው ቁም ነገርም አንጻር የደረሰው ከፍተኛ ኪሣራ ነው:: በሰነዱ ላይ በትክክል እንደተጠቀመው በሽግግሩ ዘመን አማካኝነት ለሰላም ግንባታ ተፈጥሮ የነበረውን አመቺ የታሪክ አጋጣሚ ህብረተሰባችን እንዳይጠቀምበት ተደርጓል:: ስለዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ ሲተነትን ሰነዱ የሚከተለውን ብሎ ነበር

"የሽግግሩን ዘመን የፖለቲካ ሥልጣን ከአንዱ እጅ ወደሌላ የሚሸጋገርበት ጠባብ ሂደት ብቻ አድርጎ መቁጠር ትልቅ ስህተት ነው:: አገራችንን አውተብትበው የያዟትን የጥፋት አዙሪቶች ለመስበር አስፈላጊ የሆኑትን ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ስነልቡናዊ ለውጦች በውይይት ለማስወገድ የምንጀምርበትና እንዴ ካለፈ ደግሞ ለረዥም ጊዜ የ

ማይመለስ ታሪካዊ አጋጣሚ መሆኑንም ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል ብለን እናምናለን::"

በዚህ በኩል የደረሰውን ውድቀት አሳሳቢነት ለመጠቆም በዚህ አጋጣሚ ያልተዋጋና
ቸው የሰላም ጠንቅ የሆኑ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቡናዊ አሉታዊ ቅርሶች ጊዜያቸውን
ጠብቀው የሚፈነዱ ቦንቦች ናቸው ብንል ማጋነን አይሆንብንም:: ህብረተሰቡ እንዳለ የ
ሰላምና የተሃድሶ ጥሪ በተደጋጋሚ ቢያስተላልፍም ለነዚህ ጥሪያች ሁሉ የኢህአዴግ መሪያ
ች አብሪተኛና አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል:: በዚህም የተነሳ አንዳንዶቹ የሰላም ጠንቆች
እንዳሉ ሲቀጥሉ ሌሎች ጠንቆች ደግሞ የተባባሱበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን::

እንዳሉ ሳይነኩ ቀጥለዋል የምንላቸው አጥፊ ቅርሶች ምንድን ናቸው?

የመጀመሪያውና ከሁሉም ግልጽ የሆነው በታሪካችን እንደተለመደው በጠር የበላይነ
ት የያዙ ኃይሎች ለውጥና ፍትህ ለሚፈልገው ህብረተሰብ ተገቢ ጥያቄ የሚሰጡት አብሪተኛ
መልስ ነው:: "ታግለን፣ ተሰውተን፣ አሸንፈን ለዚህ በቅተናል:: ታገሉና፣ ብረት አን
ሱና፣ ተሰውና አሸንፋችሁ ተኩን::" ይህ ነው የቀደሙት አገዛዞች ባህልና ዛሬ ለመተና
ጊዜ ኢህአዴግ በመድገም ላይ ያለው ስህተት::

ሁለተኛውና ከፍ ብለን ከጠቀስነው አብሪተኛ አቋም ጋር በጥብቅ የተያያዘው የጥ
ፋት ባህል አሸነፍን ባዮች ተሸነፉ በሚባሉት ክፍሎች አንጻር የሚከተሉት ፖለቲካ ነው::
አምባገነኖች በጠር የበላይነት አግኝተው የሚያሰፍኑት ሰላም ምንጊዜም ከወገናዊነት አል
ፍ አይሄድም:: የኢህአዴግ የሽግግር ዘመን ያመጣው ወገናዊ ሰላም ገና ከጅምሩ የኢትዮጵያ
ን ሠራዊት፣ የኢሰፖን አባላት፣ የጸጥታና የፖሊስ ኃይል አባላት፣ የሠለጠነውን የመንግሥት
ሠራተኛ ክፍል አለቃን ከጭፍራ፣ ወንጀለኛን ከንጹህ ዜጋ አደበላልቆ በጅምላ ከተሸናፊያች
ወገን የደመረና የዜግነትም ሆነ የሰብዓዊ መብት ነፍጉ ሰለባ ያደረገ ሰላም ነው::በዚህ
ም የተነሳ አንዱ በአሸናፊነት አብሪት አጉል የሚዘናናበትና የማይናቅ የህብረተሰብ ክፍል
ደግሞ በተሸናፊነት ቁጭት ጊዜና አጋጣሚ እየጠበቀ የሚያደባበት ሁኔታ ውስጥ ወድቀናል::~~ቁ~~
~~ን ደግሞ ነገሩ በዚህ አያቆምም:: የኢህአዴግ ጸረ ዲሞክራቲክ አብሪት ቀስ በቀስ በጠር~~
~~ሜዳ ያልገጠመውን አንዳንዱ እንዲያውም በስልጣን ሂደት የተባበረውን የህብረተሰብ ክፍል~~
~~እንኳን እንደተሸናፊ ቆጥሮ አገዛዙን በግድ እንደጫነ ሁሉ ከህብረተሰቡ ፍላጎት ውጭ ለመ~~
~~ቀጠል እየሞከረ እናያለን~~::

እነዚህን አሉታዊ የታሪክ ቅርሳችንን መወጣት ያልተቻለው ኢህአዴግ ይህ ያነሰ ይ
መስል በህብረተሰቡ ውስጥ እጅግ አስከፊ የሆኑ አደጋያችን የሚያመጡ አዳዲስ ጠንቆችንም
እየፈጠረ ነው:: በዚህ አንጻር ከሁሉ አስጊ ብለን የምንገምተው በሃገሪቱ ብሄረሰቦች መ
ሃከል በመንግሥት ደረጃ በጀት ተይዞለት የሚነዛው የጥላቻ ፖለቲካና መርዝ ነው::ይህ በ
ሃገራችን ነባር የሆነና እጅግ ውስብስብ ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝቦች በደማቸው እየከፈሉ ዷ
ጋራ የሆነውን አብዮታቸውን ወደፊት ያራምዱበት በነበረበት ወቅት ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ አ
ፋፍ ላይ ~~[illegible]~~ ደርሶ ነበር:: ~~በደርግ አገዛዝ እፀር ፖለቲካና በብሄር ጽንፈኞች የሚተጋገዝ የ~~
~~ጥፋት ሂደት ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ የዲሞክራሲ ትግል~~
~~እንቅፋት ሆኖ እናገኘዋለን~~::በአብዮቱ ዘመን የብሄሮች ጭቆና ምሰሶ የነበረው ያ አስከፊ
የመሬት ሥሪት በመገርሰሱ፣ በዚህም ብቻ ሳይሆን በጊዜው በግንባር ቀደምነት ተሰልፈው ይ
ታገሉ የነበሩት እንደመኢሶንና ኢህአፖ የመሳሰሉ ድርጅቶች የብሄሮችን የራስን እድል በራ
ስ የመወሰን መብት አምነው የተለያዩ ብሄሮች ታጋዮችን በህብረት አሰልፈው ይሰጡት በነበ
ረው የእኩልነትና የወንድማማችነት ምሳሌ አማካኝነት ይህ ጥያቄ የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦች
የጋራና የዲሞክራሲ ትግል የማይነጠል አካል ነበር::ዛሬ ቸግሩ አስከፊ ደረጃ ላይ ቢደር
ስ ሌላ ምክንያት የለውም::ኢህአዴግ በሚነዛውና አንዳንድ አላዋቂ ጽንፈኞች በሚነዙት የ

ጥላቻ ፖለቲካ የተነሳ በአብዮቱ ዘመን እንደነበረው የማንም ይሁን የማን ብሄር ቸግር የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ቸግር መሆኑ ተረስቷል:: ዲሞክራሲ ካለ ለሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች የሚዳረስ ማለቂያ የሌለው ጸጋ እንደሆነ፣ የአብዮቱ አፍላ አመታት እንዳላሳዩን፣ ዲሞክራሲ ለሁሉም ብሄሮች ካልተዳረሰ ደግሞ በስሙ ስለተነገደ ብቻ ለአንድ ብሄር ተለይቶ ለመንገስ እንደማይችል የወያኔን የጭቆና ቀንበር በከፍተኛ ደረጃ በመቅመስ ላይ ያለው የትግራይ ህዝብ ሁኔታ እያሳየን አሁንም የብሄርን ጥያቄ ከዲሞክራሲ ጥያቄ ለይቶ ለማየት ሲሞከር እናያለን:: ከሁሉም በላይ ደግሞ በትክክል በሰነዱ ላይ እንደተቀመጠው በእኩልነትና በዲሞክራሲ ላይ የተገነባች አንዲት አገር ውስጥ መኖር የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ብቻ ሳይሆን የመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ምኞትና ጉጉት መሆኑ እየታወቀ፣ እኩልነትና አንድነት በምንም ዓይነት የማይነጣጠሉ የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ዓላማዎች እንደሆኑ እያወቅን ሁለቱንም በጋራ እናራምዳለን የተነሱ ኃይሎች የኢህአዴግ መርዝና ምሣር ኢላማ ሆነው የሚገኙበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

ባጭሩ እንግዲህ የሽግግሩ ከፍተኛ ኪሣራ ይኸ ነው:: የኢትዮጵያን ህዝቦች ሰላም ነስተዋቸው ለዘመናት በቆዩት ፖለቲካዊና ባህላዊ ክስተቶች በተጨማሪ ኢህአዴግ የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽኦ በማድረግ ሌሎች አዳዲስና ጸረ ሰላም መርዞች በሃገራችን እየተከለ ይገኛል:: ይህንን አደጋ መዋጋት የዚህ ወይም የዚያ የፖለቲካ ድርጅት፣ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ልዩ ተልኮ አድርጎ ማቅረብ አደገኛ የዋህነት ነው:: ሃገራችንንና ህዝቦቻችንን ከጋራ ጥፋት ለማዳን የሁኔታውን አደገኛነት ተገንዝበን የኢህአዴግ አጥፊ የሽግግር ሂደት ኢትዮጵያን ለቃጠሎ ደረቱን የሰጠ የጭድ ክምር እንዳረጋት አውቀን ለጋራ ትግል መነሻው ወቅት ዛሬ ነው እንላለን::

በደንብ እንደገናም ለማንበብ ጊዜ ይሰጠናል።
እናቀይረዋለን እናስተካክለዋለን
እርዳታን
"ድርብ ተልእኮ፣ ድርብ ኪሣራ"
ብያለሁ